3.1/28/10
07 መጋቢት 2010

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
The Federal Democratic Republic
Ethiopian Revenues and Customs Authority

**በአባሪ ለተዘረዘሩት በሙሉ**
**<u>በያሉበት፣</u>**

ጉዳዩ፦ በትምህርት ሚኒስቴር የወጣው የከፍተኛ የትምህርት ወጪ መጋራት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2009 አተገባበር ይመለከታል፣

የኢ.ፌ.ድ.ሪ የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ክፍያን አስመልክቶ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (2) በተሰጠዉ ሥልጣን መሰረት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2004ን አሻሽሎ ከነሐሴ 24 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ የፀና የከፍተኛ የትምህርት ወጪ መጋራት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2009 በማውጣት ስራ ላይ እንዲውል በቁጥር 7/ጠ159/11179/35 በ25/12/2009 ዓ/ም በተጻፈ የተላከውን ለአፈጻጸም እንዲረዳ ከዳይሬክቶሬታችን በቁጥር 3.5.0/28/10 መስከረም 26 ቀን 2010 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ መላኩ ይታወሳል፡፡

የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ወጪ መጋራት ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ (5) በተሰጠዉ ሥልጣን መሠረት ወጪ መጋራት ከገንዘብ በተለየ መልኩ በአገልግሎት የሚፈጽሙትን መስኮችና ዝርዝር መመሪያዎች የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም መሠረት በመመሪያ ቁጥር 02/2009 አንቀጽ 6.12 በማናቸውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በመንግስት ትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ፣ በመምህራን ማሰልጠኛ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሟት፣ በሌሎች የመንግስት የማሰልጠኛ ኢኒስቲትዩት በመምህርነት ሙያ ወይም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኝነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል እና ማረሚያ ቤቶች በፖሊስ ሰራዊት አባል የሆኑ ብቻ በምደባም ይሁን በቅጥር በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራት በአገልግሎት ሊያዘላቸው ይችላል፡፡ ሆኖም ግን በከፊል አገልግሎት ሰጥተው ካቋረጡ ቀሪዉን የወጪ መጋራት ግዴታቸውን ከነመቀጫው ገንዘብ በመክፈል እንዲወጡ ይደረጋል በሚል ሰፍሯል፡፡

ይሁን እንጂ የተሻሻለው የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 02/2009 ለአፈጻጸም ሲተባበፍ አንቀጽ 6.13 በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል፣በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል እና ማረሚያ ቤቶች በፖሊስ ሰራዊት አባልነት አገልግሎት እየሰጡ ያሉ አገልግሎት ከሰጡበት ተቋም በሚያቀርቡት ማስረጃ መሰረት በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከእዳ ነጻ ስለመሆናቸው ከባለስልጣኑ ማስረጃ በማቅረብ የትምህርት ማስረጃቸውን ከተማሩበት የትምህርት ተቋም ማግኘት እንደሚችሉ የተገለጸ በመሆኑ፡-

1. በክፍያ የወጪ መጋራት ውል የገቡና የመመሪያው ማሻሻያ ከመውጣቱ በፊት የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በገንዘብ መወጣት የሚኖርባቸው የመከላከያ ሰራዊትና የፖሊስ አባላት በተለያየ ምክንያት ክፍያ ሳይፈጽሙ ቆይተው መመሪያው መውጣቱን ተከትሎ ግዴታችንን በአገልግሎት የተወጣን በመሆኑ ማስረጃ ይሰጠን በማለት፣
2. በመከላከያ ሰራዊት እና በፖሊስ አባልነት ላይ እየሰሩ ያሉ የማሻሻያው መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የትምህርት ማስረጃና ሌሎች አገልግሎቶች ለማግኘት የሚፈለግባቸውን የወጪ መጋራት ክፍያ ፈጽመው እዳ እንደሌለባቸው የምስክር ወረቀት በወቅቱ የተሰጣቸው ወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የመመሪያውን መሻሻል መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል የከፈሉት ክፍያ ተመላሽ ይደረግልን፣ የሚሉ ጥያቄዎችን ቀርበዋል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የማሻሻያ መመሪያው የተፈጻሚነት ወሰን ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ ወደ መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ እንዲሁም የሁለተኛ እና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን የተገለጸ ቢሆንም መመሪያው ከነሐሴ 24/2009 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል የሚል በመሆኑ በዚህ አግባብ እንደሚስተናገዱ ቢገለጽላቸውም ቅሬታ በማቅረባቸው ምክንያት አገልግሎቱን ለመስጠት ክፍተት በመፈጠሩ ትምህርት ሚኒስቴር ስለመመሪያው አተገባበር ግልጽ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ጥቅምት 17 ቀን 2010 ዓ/ም በቁጥር 3.5.0/37/10 በተጻፈ ደብዳቤ ተጠይቋል፡፡

ከሚኒስትር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ስራ ክፍሎች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት ከተደረገ በኃላ በቁጥር 17/ጠ259/4179/10 በ3/5/2010 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በመመሪያው የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በአገልግሎት እንዲወጡ አዲስ የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች መመሪያው ስራ ላይ ከዋለበት ከነሐሴ 24 ቀን 2009 ዓ/ም ጀምሮ ስለመሆኑ፣

1. በመመሪያው አንቀጽ 6 (6.4፣ 6.11፣ እና 6.12) መሰረት በመንግስት የትምህርትና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና ፈጻሚ ሰራተኝነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በክልል እና ማረሚያ ቤቶች በፖሊስ ሰራዊት አባል የሆኑ ብቻ ተመድበው ወይም ሳይመደቡ በራሳቸው

ጥረት ተቀጥረው በማገልገል ላይ ያሉ ቀደም ሲል የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በክፍያ ለመወጣት ውል የፈጸሙ ቢሆንም ለሰለጠኑበት /ለተማሩበት/ ጊዜ እኩል የአገልግሎት ጊዜ በመስጠት ግዴታቸውን በአገልግሎት መወጣት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን መመሪያው ስራ ላይ ከመዋሉ ከነሀሴ 24/2009 በፊት የተሰጠው አገልግሎት ታሳቢ አይደረግም፡፡

2. በአፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 6(6.11) ተጠቃሚው ቀደም ሲል በሌላ መስክ ተሰማርቶ በገንዘብ መክፈል የጀመረ ከሆነ ቀሪውን የክፍያ መጠን ብቻ መንግስት በሚመድበው ቦታ በአገልግሎት እንዲወጣ በተገለጸው መሰረት የሚተገበር ሆኖ ከዚህ ቀደም ተጠቃሚው የከፈለው ገንዘብ ተመላሽ አይደረግም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም የወጪ መጋራት ክፍያን በአገልግሎት የሚወጡ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ በገቢ ሰብሳቢ ቅ/ጽ/ቤቶች ወጥ አረዳድ እና አፈጻጸም እንዲኖር ለማስቻል በመመሪያ ቁጥር 01/2004 እና በመመሪያ ቁጥር 02/2009 ያለውን ልዩነት በተመለከተ ግልጽ ለማድረግ ከዚህ እንደሚከተለው በማነጻጸር ቀርቧል፡፡

1. መመሪያ ቁጥር 01/2004 አንቀጽ 6
   - ✓ ንኡስ አንቀጽ 6.8 በትምህርት ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ ማንኛውም የመንግስት ትምህርት ቤት፣ የቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ ፣ የመምህራን ማሰልጠኛ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በሌሎች የመንግስት የማሰልጠኛ ኢንስቲትውት ተመድቦ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡ ምደባ ካላገኘም ለሚመለከተው አካል በወቅቱ በማስታወቅ መረጃ መያዝ ይኖርበታል፡፡ (ለክልል ትምህርት ቢሮ ወይም ለትምህርት ሚኒስቴር) በሚያቀርበው መረጃ መሰረት በማድረግ የወጪ መጋራቱን በገንዘብ እንዲወጣ እንደሚደረግ፣
   - ✓ ንኡስ አንቀጽ 6.9 በጤና ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በሚመድበው ማንኛውም በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኝ የመንግስት የጤና ተቋማት አገልግሎት የመስጠት ግዴታ ሲኖርበት ምደባ ከአላገኘም ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ማስረጃ በመያዝ የወጪ መጋራት ክፍያ ግዴታውን በገንዘብ እንዲወጣ እንደሚደረግ፣
   - ✓ ንኡስ አንቀጽ 6.10 በትምህርት ሙያ መስክ ሳይሰለጥኑ በምደባም ሆነ በቅጥር በመምህርነት ሙያ ከላይ በተራ ቁጥር 6.8 በተጠቀሱት በመንግስት ተቋማት በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራቱ በአገልግሎት ሊያዝላቸው እንደማችልይገልጻል ::

ይህም በተሻሻለው መመሪያ ቁጥር 02/2009 አንቀጽ 6 (8) እና (9) የተጠቀሰው በትምህርት ሙያ የሰለጠነ እና በጤና ሙያ የሰለጠነ ተጠቃሚ በመንግስት ተቋማት ተመድቦ የወጪ

መጋራት ግዴታውን በአገልግሎት መስጠት ግዴታ ያለበት ሲሆን ምደባ ካላገኘም ለሚመለከተው አካል በማሳወቅ (ቀደም ሲል ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ብቻ የነበረው በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ጤና ቢሮ በሚል ከመካተቱ በስተቀር) መረጃ በመያዝ እና በማቅረብ የወጪ መጋራቱን በገንዘብ እንዲወጣ እንደሚደረግ በተመሳሳይ የተገለጸው እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡ በዚህም መመሪያ መሠረት ምደባ ያላገኙ ከሆነ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ጤና ቢሮ የሚጻፉ መረጃዎች ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

2. መመሪያ ቁጥር 02/2009 አንቀጽ 6

   - ✓ ንኡስ አንቀጽ (6.12) በማንኛውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በመንግስት የትምህርት ቤቶች፣ በቴክኒክ ሙያ ማሰልጠኛ፣ በመምህራን ማሰልጠኛ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በሌሎች የመንግስት ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በመምህርነት ሙያ ወይም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶች እና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኝነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌደራል፣ በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል እና ማረሚያ ቤቶች ፖሊስ ሠራዊት አባል የሆኑ ብቻ በምደባም ይሁን በቅጥር በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራቱ በአገልግሎት ሊያዝላቸው እንደሚችል፤ ሆኖም ግን በከፊል አገልግሎት ሰጥተው ካቋረጡ ቀሪውን የወጪ መጋራት ግዴታቸውን ከነመቀጫው ገንዘብ በመክፈል እንደሚወጡ ይገልጻል፡፡

ስለሆነም በማንኛውም የትምህርት መስክ ተመርቀው በመንግስት ተቋማት በመምህርነት ሙያ እና በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶች በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኝነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት እና በፖሊስ ሰራዊት አባልነት በምደባም ይሁን በቅጥር በማገልገል የሚገኙ መመሪያ ቁጥር 2/2009 ከመውጣቱ በፊት በነበረው መመሪያ መሰረት የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በክፍያ ለመወጣት ተስማምተው ክፍያ እየፈጸሙ የሚገኙ ወይም ክፍለው ያጠናቀቁ ወይም ክፍያ ሳይፈጽሙ የቆዩ አዲሱ መመሪያ ከወጣ በኋላ የሚሰጡት አገልግሎት እንደሚያዝላቸው ይሁን እንጂ ሙሉ ክፍያ ያላጠናቀቁ ቀሪውን ጊዜ በአገልግሎት እንደሚያዝላቸው ሆኖ፣ መመሪያው ከመሻሻሉ በፊት የከፈሉት ክፍያ እንዲመለስላቸው እንዲሁም ቀደም ሲል የሰጡት አገልግሎት እንዲያዝላቸው የሚቀርቡ ጥያቄዎች ተቀባይነት የለውም፡፡

በሀገር መከላከያ ሰራዊትና በፖሊስ ሰራዊት አባልነት የሚያገለግሉ ከሚያከናውኑት የስራ ክብደትና አስቸጋሪነት እንዲሁም ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ሊጣጣም የሚችል ብቁ የሰው ኃይል በመስኩ ከማስማራትና ሀገራዊ ተልዕኮን ከመፈጸም አንጻር አባላቱን ለማበረታታት እንዲሁም በመንግሰት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በኃላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት የሚያገለግሉ አካላት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እና የጤና ግቦች ለማሳካት

ብሎም ወደነዚህ የስራ መስኮች የተማረ የሰው ሀይል የሚሳብበትንና የሚቆይበት አግባብ እንዲኖር በነዚህ የስራ መስኮች በማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በአገልግሎት እንዲወጡ የተፈቀደ መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም በተሻሻለው መመሪያ መሠረት የጤና ባለሙያዎች ሆነው ምደባ ያላገኙ ከሆነ አዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ በክልል ጤና ቢሮ የሚጻፉ መረጃዎች ተቀባይነት የሚኖረው መሆኑን እንዲሁም የወጪ መጋራት በአገልግሎት እንዲያዝላቸው አዲስ ከተፈቀደላቸው የሚቀርቡ ጥያቄዎች አውቀዉ በተገቢው ሁኔታ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎችና ሰራተኞች እና በተሻሻለው መመሪያ በአገልግሎት እንዲያዝላቸው የተፈቀደላቸው በክልልና ከተማ አስተዳደር የመንግስት መ/ቤቶች እንዲያውቁት መመሪያው ከነማብራሪያው እንዲደርሳቸው እንዲደረግ እያሳሰብን፣ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በቁጥር 17/ጠ259/4179/10 በ3/5/2010 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የተላከውን ማብራሪያ ከነመሸኛው 3 ገጽ ፎቶ ኮፒ አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን። የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች እና ቀጣሪዎች እንዲያውቁት በባለስልጣኑ ድረ-ገጽ (Website) እንዲጫን የዚህ ደብዳቤ ግልባጭ ለኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት እንዲደርሳቸው ተደርጓል።

ከሰላምታ ጋር

አባይነሽ አባተ
የሀገር ውስጥ ታክስ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፦
- ለአገር ውስጥ ታክስ ዘርፍ
- ለኦዲት አሠራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ አስተዳደር ማጣጣምና የክልሎች ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት
- ለታክስና ጉምሩክ መረጃ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ልማትና አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- ለህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- ለኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

- ለትምህርት ሚኒስቴር
- ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- ለመከላከያ ሚኒስቴር
- ለፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር
- ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

አዲስ አበባ

21/5/10

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የትምህርት ሚኒስቴር
# Ministry of Education
# Federal Democratic Republic of Ethiopia

ቀን / Date: 3/5/2010
ቁጥር / Ref: 17/መ2ሰ9/4179/10

ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2009 ዓ.ም ላይ ማብራሪያ መስጠትን ይመለከታል**

የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2009 ስራ ላይ መዋሉንና መመሪያው ከ1996 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ መንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ተፈጻሚ መሆን ጋር ተያይዞ የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በአገልግሎት እንዲወጡ በተፈቀደላቸው አዲስ የሙያ መስኮች ላይ በማገልገል ላይ ካሉ አንዳንድ ተጠቃሚዎች1ኛ) ግዴታቸውን በገንዘብ መወጣት የነበረባቸው ክፍያ ሳይፈጽሙ ቆይተው ግዴታቸውን በአገለግሎት ተወጥተናል ማስረጃ ይሰጠን የሚል ጥያቄ ስለሚያቀርቡ 2ኛ) መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የወጪ መጋራት አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚፈለግባቸውን ክፍያ ፈጽመው ዕዳ እንደሌለባቸው የምስክር ወረቀት በወቅቱ የተሰጣቸው የከፈሉት ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግላቸው ጥያቄ ስለሚያቀርቡ አገልግሎቱን ለመስጠት መቸገራችሁን ገልጻችሁ በመመሪያው አተገባበር ላይማብራሪያ እንድንሰጣችሁ በቁጥር 3.5.0/37/10 በቀን ጥቅምት 17ቀን 2010 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል:: በዚሁ መሰረት ከዚህ በታች 2 ገጽ ማብራሪያ ሰጥተናል::

ከሰላምታ ጋር

[signature] ... መስፍን ... (ዶ/ር)
... ትም/አስተዳደር ...
ጀኔራል ዳይሬክተር

ግልባጭ

- ለከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለከፍተኛ ትም/አስ/ጉዳዮች ጀኔራል ዳይሬክቶሬት

ትምህርትሚኒስቴር

ራዕያችን ብቁ ዜጋ የሚያፈራ፣ ጥራትና ፍትሃዊነት ያረጋገጠ የትምህርትና ስልጠና ስርዓት በቀጣይነት መገንባት ነው!

አዲስ አበባ / Addis Ababa
+251 11 1553133
ፋክስ / Fax +251 11 1570686
ፖ.ሳ.ቁ. 1367
Commu@moe.gov.et
www.moe.et www.facebook.com/ fdremoe

**<u>በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 02/2009 ዓ.ም ላይ ማብራሪያ ስለመስጠት</u>**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 154/2000 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በሀገር መከላከያ ሰራዊትና በፖሊስ ሰራዊት አባልነት የሚያገለግሉ ከሚያከናውኑት የስራ ክብደትና አስቸጋሪነት እንዲሁም ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር ሊጣጣም የሚችል ብቁ የሰው ሀይል በመስኩ ከማሰማራትና ሀገራዊ ተልዕኮን ከመፈጸም አንጻር አባላቱን ለማበረታታት እንዲሁም በመንግስት የትምህርት እና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና በፈጻሚ ሰራተኛነት የሚያገለግሉ አካላት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ እና የጤና ግቦች ለማሳካት ብሎም ወደነዚህ የስራ መስኮች የተማረ የሰው ሀይል የሚሳብበትንና የሚቆይበት አግባብ እንዲኖር በነዚህ የስራ መስኮችበማገልገል ላይ ያሉ የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በአገልግሎት እንዲወጡበማካተት ቀደም ሲል ሥራ ላይ የነበረው አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2004 ተሻሽሎ በመመሪያ ቁጥር 02/2009 የተተካ ሲሆን ከነሐሴ 24/2009 ዓ.ም ጀምሮ ስራ ላይ ውሏል።

በመመሪያው አንቀጽ 10 በተደነገገው መሠረት ከወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብም ሆነ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ክፍያ አሰባሰብ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 001/2004 በመመሪያ 02/2009 የተተካ በመሆኑ ከ1996 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ጀምሮ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በገቡ አዲስ ተማሪዎች እንዲሁም የሁለተኛ ዓመትና ከዚያ በላይ በሆኑ ነባር ተማሪዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል ።

በመመሪያው የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በአገልግሎት እንዲወጡ አዲስ የተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች መመሪያው ስራ ላይ ከዋለበት ከነሐሴ 24/2009 ዓ.ም ጀምሮ ፡

1ኛ) በመመሪያው አንቀጽ 6(6.4፣6.11 እና 6.12) መሠረት በመንግስት የትምህርትና ጤና ሴክተር መስሪያ ቤቶችና ተቋማት በሀላፊነትና ፈጻሚ ሰራተኛነት እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሰራዊት በፌደራል በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር በክልል እና ማረሚያ ቤቶች

በፖሊስ ሰራዊት አባል የሆኑ ብቻ ተመድበው ወይም ሳይመደቡ-በራሳቸው ጥረት ተቀጥረው በማገልገል ላይ ያሉ ቀደም ሲል የወጪ መጋራት ግዴታቸውን በክፍያ ለመወጣት ውል የፈጸሙ ቢሆንም ለሰለጠኑበት /ለተማሩበት/ ጊዜ እኩል የአገልግሎት ጊዜ በመስጠት ግዴታቸውን በአገልግሎት መወጣት ይችላሉ ::ነገር ግን መመሪያው ስራ ላይ ከመዋሉ ከነሐሴ 24/2009 በፊት የተሰጠ አገልግሎት ታሳቢ አይደረግም::

2ኛ) በአፈጻጸም መመሪያው አንቀጽ 6(6.11) ተጠቃሚው ቀደም ሲል በሌላ መስክ ተሰማርቶ በገንዘብ መክፈል የጀመረ ከሆነ ቀሪውን የክፍያ መጠን ብቻ መንግስት በሚመድበው ቦታ በአገልግሎት እንደሚወጣ በተገለጸው መሠረት የሚተገበር ሆኖ ከዚህ ቀደም ተጠቃሚው የከፈለው ገንዘብ ተመላሽ አይደረግም::